Letter to Parents CARE Project (Amharic)

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

American Academy of Pediatrics
DEDICATED TO THE HEALTH OF ALL CHILDREN™
DISTRICT OF COLUMBIA CHAPTER

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
DOH
DEPARTMENT OF HEALTH
Promote. Prevent. Protect.

መጋቢት (March) 16, 2017

ውድ የዲሲፒኤስ ( DCPS) ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና  ቤተሰቦች፤

በዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS)፣ ለተማሪዎቻችን ጤንነት እና ደህንነት ዋጋ እንሰጣለን። ጤናማ የሆኑ ተማሪዎች ትምህርት ቤት እየተገኙ የተሻለ እንደሚማሩ እናውቃለን። የተማሪዎቻችን ጤንነት እና ከትምህርት ቤት መገኘትን ከሚደግፍ ፕሮጀክት ዲሲፒኤስ፣ ከአካባቢ ዶክተሮች፣ ነርሶች፡ እና ከዲሲ የጤና መመሪያ ጋር ቅንጅታዊ ትብብር ስለማድረጉ የምንገልጸው በደስታ ነው። ይህ ፕሮጀክችት በቀጣዩ  2017-2018 የትምህርት ዓመት ይጀመራል።

በፕሮጀችቱ አማካይነት -- ሥር የሰደደ ከትምህርት ገበታ መለየትን የማሰቀነስ ጥረት (the **C**hronic **A**bsenteeism **R**eduction **E**ffort or **CARE**)) – በአጭሩ **CARE** ተብሎ በሚጠራው አማካይነት-- ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች፣ ከትምህርት ገበታ ላይ ስለመገኘት መረጃዎችን ከልጃቸው ዶክተር(ሮች)፣ ነርስ(ሶች)፣ እና ከህክምና ጽሕፈት ቤት ባለሙያዎች ጋር አስተማማኝነት ባለው ሁኔታ ሀሳብ በምሥጢር እንዲለዋወጡ ለዲሲፒኤስ (DCPS) ፈቃድ መስጠት ይችላሉ። ይህ መረጃም፣ እነዚህ የጤና ጥበቃ ባለሙያዎች፣ ከትምህርት ቤት እና ከወላጆቻቸው የሚቀሩ ልጆችን ሁሉ ለማዳረስ (outreach) የህክምና እርዳታ ለማድረግ የሚረዳ ነው።

**ለምንድን ነው ዲሲፒኤሲ ( DCPS) እና የአካባቢ ዶክተሮች እና ነርሶች በዚህ ፕሮጀክት ላይ የሚሳተፉት?**
ዲሲፒኤስ እና የአካባቢ ጤና ጠባቂዎች፣ ትምህርት ቤት የሌሉ ልጆች፣ አካላዊ እና አእምሮአዊ ጤንነታቸውተጠብቆ ለመማር ዝግጁ ሆነው በየዕለቱ ከትምህርት ቤት እንዲገኙ የማድርገ ግብን በጋራ ይጋራሉ። እንደ አስም፣ አለርጂ፣ ሲክል ሴል አኒሚያ (sickle cell anemia) እና የስኳር በሽታ የመሳሰሉ የጤንነት ሁኔታዎች ለአብዛኛዎቹ በርካታ ተማሪዎች አስቸጋሪ ሊሆኑ ይችላሉ። ዲሲፒኤስ እና የአካባቢ ዶክተሮች፣ ነርሶች ትምህርት ገበታ ላይ ስለመገኘት የበለጠ ቢያውቁ ተማሪዎችን በጤንነት እና በደህንነታቸው በተሻለ ሁኔታ ይደግፉ እንደሆነ ለማየት ነው። በመጨረሻም፣ ይህ፡ ተማሪዎች ትምህርቶቻቸውን ለማሻሻል እንደሚረዳ ተስፋ እናደርጋለን።

**ይህ ፕሮጀችት ልጄን የሚረዳው እንዴት ነው?**
ልጅዎ፣ ከትምህርት ቤት ይቀር እንደሆነ ዶክተሮች፣ ነርሶች፣ እና አባል ሠራተኞቻቸው ልዩ ሁሉንም የማዳረስ እርዳታ እና የህክምና ድጋፍ ማድረግ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ የልጅዎ ዶክተር፣ ልጅዎ የተሻለ ጤንነት እንዲሰማው እና አስሙን፣ አለርጅዎን፣ እና ሌሎችም ሁኔታዎችን በተሻለ መልክ ለመቆጣጠር አዲስ ወይንም የተለየ መድኃኒት ሊያዝለት ይችላል። ህክምና ሰጪው ቡድን ልጅዎ ትምህርት ቤት ለመሄድ የሚረዱትን እንደ መጓጓዣ ለልጁ ደህንነት የሚያስፈልጉ ሌሎች ተራ የሆኑ ጉዳዮችን ለመደገፍ የሚያስችሉ ነገሮችን ሊያዝለት ይችላል።

**የትኞቹ ትምህርት ቤቶች ናቸው የሚሳተፉ?**
ለ 2017-2018 የትምህርት ዓመት፣ ዲሲፒኤስ ይህንን ፕሮግራም በጥናት መልክ በባንክሮፍት (Bancroft Elementary) አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በካርዶዞ የትምህርት ምድረ ግቢ (Cardozo Education Campus)፣ በኮሎምቢያ ሀይትስ የትምህርት ቅጥር ግቢ (Columbia Heights Education Campus)፣ በኤች ዲ ኩክ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (H.D. Cooke Elementary)፣ ሜሪ ሪድ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Marie Reed Elementary)፣ እና ፓውል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Powell Elementary) ይካሄዳል። እነዚህ ትምህርት ቤቶች የተመረጡበት ዋናው ምክንያት፣ በእነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች የህክምና አገልግሎቶቻቸውን የሚያገኙት በአንድ ዶክተር የጤና አገልግሎት ጽሕፈት ቤት አማካይነት በመሆኑ ነው። ይህም ዲሲፒኤስ፣ ከእነዚህ ዶክተሮች እና ነርሶችጋር በጣም ጠንካራ በሆነ ሁኔታ እንዲሳተፍ ስለሚያስችል ነው።

**የምፈርመው እንዴት ነው?**
ለመፈረም፣ ከዚህ ጋር ተያይዞ በቀረበውን የስምምነት መግለጫ ቅጽ ላይ ፊርማውዎን በማስፈር ለልጅዎ ትምህርት ቤት  የምዝገባ ክፍል ኃላፊ እባክዎን ያስረክቡ።

**የበለጠ መማር የምችለው እንዴት ነው?**
ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን ከልጅዎ ትምህርት ቤት የምዝገባ ክፍል ኃላፊው ፣ ከትምህርት ቤቱ ነርስ፣ ወይንም ጤና ጠባቂው ጋር ይነጋገሩ። በተጨማሪም የዲሲፒኤስ የጤና ኣና የደህንነት ቡድን ን በ healthservices.dcps@dc.gov ወይንም  202.719.6555 አማካይነት መገናኘት ይችላሉ። ተዘውትረው የሚጠየቁ ጥያቄዎች ሠነድ በ  http://dcps.dc.gov/page/health-and-wellness ላይ ይገኛል።

ከልባዊ ሠላምታ ጋር፤


Heidi Schumacher, MD, FAAP
Deputy Chief, Student Wellness
DC Public Schools

Marcee White, MD, FAAP
President
DC Chapter, American Academy of Pediatrics

Anjali Talwalkar, MD, MPH
Senior Deputy Director
DC Department of Health